የሰ/መ/ቁ. 40938

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይዝ - ነ/ፈጅ ሰይፉ በቀለ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ኃይሉ መንግስቱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ህዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም የፃፉት ማመልከቻ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከጥቅምት 22 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ በቅጥር ላይ በተመሰረተ ግንኙነት በጥበቃ ኃላፊነት የስራ መደብ ተመድበው እየሰሩ ባሉበት ሁኔታ ከህብረት ስምምነቱ ውጪ ከጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ድርጅት በፃፈው ደብዳቤ የስራ መደቡን ወደ ማይገለጽ በቅርብ ኃላፊ በሚሰጥ ትእዛዝ መሰረት ብቻ እንዲሰሩ ገልፆ ያዛወራቸው መሆኑን በመዘርዘር የስራ መደብ ዝውውሩ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ወደ ጥበቃ ኃላፊነት የስራ መደብ ተመልሰው እንዲሰሩ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአመልካች ድርጅት ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ አመልካች ድርጅትም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መከላከያ መልስ ተጠሪ የጥበቃ የኃላፊነት ስራ ባግባቡ ስላልተወጡና ጉዳዩ ተጣርቶ ለሕግ እስኪቀርብ ድረስ ከስራ ደረጃቸውና ከደመወዛቸው ሣይቀንስ ወደ አቻ ሌላ የስራ ቦታ ማዛወሩ ህጋዊ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የተጠሪ የስራ መደብ ዝውውር ከህጉ አግባብ ውጪ ነው በማለት ተጠሪ በፊት ይሰሩበት የነበረውን የጥበቃ ኃላፊ ይዘው እንዲሰሩ ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ተወካይ ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ከፃፉት 3/ሦስት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ የግራ ቀኙ የቃል ክርክርም መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበትና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች የተጠሪ የስራ ደረጃና ደመወዛቸውን ማይቀንስ የስራ መደቡን ዝውውር መፈፀሙ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተጠሪ በቀድሞ የስራ መደብ ተመድበው እንዲሰሩ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የተጠሪ የስራ ደረጃና ደመወዛቸው ሣይቀንስ አመልካች ተጠሪን ከጥበቃ ኃላፊነት የስራ መደብ በማንሣት እያሰራ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በጥበቃ ኃላፊነት ያገኙ የነበሩትን ደመወዝ

አሁንም እያገኙ ያሉ መሆኑን ሣይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት የሚሰሩበት የስራ መደብ በመዋቅሩ የማይቃወቅ መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡

በመሰረቱ አሰሪ የሰራተኛውን ደረጃ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ሣይነካ ከአንዱ የስራ መደብ ወደ ሌላ ተመሳሳይ የስራ መደብ አዛውሮ ማሰራት ከተቋሙ አደረጃጀትና ከአሰሪነት መብቱ የሚመነጭ መብት ነው፡፡ የአሰሪ መዋቅርና አደረጃጀት እንዲሁም የሰራተኛን መብት በማይነካ ሁኔታ ሰራተኛን ከአንድ የስራ መደብ ወደ ሌላ በተመሣሣይ የስራ መደብ አዛውሮ ማሰራት ህገ ወጥ የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የስራ መደብ ዝውውር ስራና ሰራተኛን ለማገናኘት ወይም ስራው እንዳይበደል ታስቦና ተረጋግጦ ከተፈጸመ ህገ ወጥ ሊባል አይችልም፡፡ ይልቁንም የኢንዱስትሪ ሰላምን ይፈጥራል፣ ለሐገር ሁለንተናዊ እድገትና ልማት አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ የአሰሪን ድርጅት መዋቅርና አደረጃጀት እንዲሁም የሰራተኛውን ጥቅም የጠበቀ ትእዛዝ የመፈጸምና የማክበር ግዴታ ይኖረዋል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13/2/ እና /7/ ድንጋጌዎች ይዘት የሚያስገነዝበውም ይህንኑ ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ተጠሪን ያዛወረው ከድርጅቱ መዋቅርና አደረጃጀት ውጪ እንዲሁም የተጠሪን ጥቅም ባልጠበቀ ሁኔታ ስለመሆኑ ሣይረጋገጥ አመልካች ተጠሪን በፊት ይሰሩበት በነበረው በደረጃ 10 የጥበቃ ኃላፊ የስራ መደብ ይመልሰው በማለት መወሰናቸውን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 29948 ሚያዝያ 29 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 67189 ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የድርጅቱን መዋቅርና አደረጃጀት እንዲሁም የሰራተኛውን መብት በጠበቀ ሁኔታ አንድን ሰራተኛ ከአንድ የስራ መደብ ወደ ሌላ ተመሣሣይ የስራ መደብ የማዛወር ሕጋዊ መብት ስላለው በተጠሪ ላይ የፈፀመው ተግባር ሕገ ወጥ አይደለም ብለናል፡፡
3. ተጠሪን ወደ ደረጃ 10 የጥበቃ ኃላፊ የስራ መደብ አመልካች እንዲመልሰው የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ